**የዳራ ሰነድ**

# በኢትዮጵያ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት

UN WOMEN

© 2022. ዩኤን ውመን. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው.

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ክፍል የኢትዮጵያ ቢሮ (ዩኤን ውመን) የተዘጋጀ።

በዚህ ኅትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የጸሐፊው(ዎች) ናቸው እንጂ የግድ የተባበሩት መንግስታት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና ሴቶችን የማብቃት ክፍል (የዩኤን ውመን)፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ወይም ማንኛውንም ተዛማጅ ድርጅቶችን አስተያየት አይወክልም።

የዳራ ሰነድ

# በኢትዮጵያ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት



**ዩኤን ውመን.የኢትዮጵያ ቢሮ**
አዲስ አበባ, ነሃሴ 2022 (እ.ኤ.አ.)

# ማውጫ

**1. በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ምንድን ነው?** 5

**2. የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት ሂደት**

ዋና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን መለየት እና ግብረ ሃይል ማቋቋም

ፍላጎቶችን ለመለየት ጥናቶችን እና ምዘናዎችን ማካሄድ

ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክሮች እና የሲቪል ማህበረሰብን ተሳትፎ ማረጋገጥ

ለትግበራ፣ ለክትትልና ለግምገማ አወቃቀሮችን ማዘጋጀት

በቂ የሀብት (Resource) ድልድልን ማረጋገጥ

የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የሂደት መዘርዝር ምሳሌዎች

**3. የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን ያለ ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር መተግበር**

**4. በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ላይ ያሉ ችግሮች እና የመውጫ መንገዶች** 11

**5. በኢትዮጵያ በቀጣይ መሰራት ያለበት** 13

**የንባብ ዝርዝር** 15

## 1. በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ምንድን ነው?

ሴቶች ለዘመናት ከሰላምና ጸጥታ ዘርፎች ተገልለው ቆይተዋል። ምንም እንኳን ግማሹን የዓለም ሕዝብ የሚወክሉ ቢሆኑም፣ ሴቶች በብሔራዊ እና በዓለም አቀፍ የጸጥታ ኃይሎች ውስጥ ያላቸው ውክልና እጅግ ዝቅተኛ ነው፤ በሰላም ድርድር መድረኮች ላይ ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ የሉበትም፤ በእርዳታ እና ከግጭት በኋላ መልሶ መገንባት እና ማገገም ተግባራት ተገቢውን አገልግሎት አላገኙም፤ በሕግ አውጪ እና በሌሎች የውሳኔ ሰጪ መዋቅሮች ውስጥ ያላቸው ውክልናም አነስተኛ ሲሆን በተለይም በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ ለጾታዊ ጥቃት የተጋለጡ ናቸው። በተጨማሪም፣ አስታራቂዎች፣ ወታደሮች እና ደጋፊዎች በመሆን በሰላምና በፀጥታ ላይ ያላቸው ሁለ-ገብ ሚና በአለም አቀፍ እና በአገራዊ ውሳኔ አሰጣጥላይ በበቂ ሁኔታ እውቅና አላገኘም።[1] የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ይህንን ችግር ለመፍታት ያለመ ነው።

የተባበሩት መንግስታት (የተመድ) የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔ 1325 (2000 እ.ኤ.አ) እና የዚህ ተከታይ ውሳኔዎች[2] የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ተብሎ የሚጠራውን ዓለም አቀፍ ማዕቀፍ ፈጥሯል። የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ በሁሉም ደረጃዎች የሰላምና ጸጥታ አስተዳደርን ለማስፈን የሴቶች ሁለንተናዊ እና እኩል ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ፣ በትጥቅ ግጭቶች ወቅትም ሆነ በኋላ ሴቶችንና ልጃገረዶችን መከላከል እንደሚያስፈልግ እና የሥርዓተ-ፆታ አመለካከትን በሁሉም ከሰላምና ጸጥታ ጋር በተያያዙ ሂደቶች የማቀድ፣የመተግበርና የመከታተል ስራዎች ላይ ተግባራዊ የማድረግ አስፈላጊነትን ይገነዘባል።አጀንዳው ግጭትን ለመከላከል እና ለመፍታት የአጠቃላይ አቀራረብ አስፈላጊ አካል ነው።

ይህም በሚከተሉት አራት ምሰሶዎች አማካይነት ይቀርባል፡-

• ሰላምን ከመፍጠር እና ከመገንባት ጋር በተያያዙ ሰላማዊ ሂደቶች እና በሁሉም ህዝባዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ የሴቶች **ተሳትፎ**

• በቅድሚያ ማስጠንቀቅ ስርዓቶች፣ በህዝባዊ ትምህርት እና የሴቶችን መብቶች የሚጥሱ ወንጀለኞችን ለህግ በማቅረብ ረገድ የሴቶችን አመለካከቶች በማካተት ግጭትን **መከላከል**

• ለሴቶች በግጭት ወቅት እና ከግጭት በኋላ በማህበረሰብ፣ በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ የጸጥታ አካላት አማካኝነት **ጥበቃ ማድረግ**

• ሴቶችን ያሳተፈ እና ፍላጎቶቻቸውን የሚፈታ እና በኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዋስትና ላይ ኢንቨስት የሚያደርግ **እርዳታ እና ከግጭት በኋላ መልሶ መገንባት እና ማገገም**

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሀገራት የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን በመተግበር ረገድ ቁልፍ ተዋናዮች ናቸው። በተጨማሪም ብሄራዊ ፖሊሲዎች፣ ህጎች እና የበጀት ሂደቶች ሃገራቱ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ከገቧቸው አለም አቀፍ ቃል ኪዳኖች እና ግዴታዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን የማረጋገጥ ተቀዳሚ ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት አባል ሀገራት ቃል ኪዳናቸውን ወደ ተግባር ለመቀየር ስትራቴጂዎችን እና ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮችን እንዲፈጥሩ ጥሪ አቅርቧል[3]። በመሆኑም፣ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች (እንዲሁም የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ወይም ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር 1325 በመባል ይታወቃሉ) የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን አፈፃፀም መምራት ያለባቸው መሳሪያዎች ናቸው።

ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የአለም አቀፍ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ቃል ኪዳኖችን ወደ አካባቢያዊ እና አገራዊ ተግባር ለመተርጎም የሚሆን መሳሪያ ነው። መርሃ ግብሩ በተቀመጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ የመንግስትን ወቅታዊ እና የወደፊት ተግባራትን ያካትታል። ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እና ኃላፊነቶችን የሚለይ እና ለሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ትግበራ የሚያስፈልጉ ሃብታትን (resources) የሚመድብ ሰነድ ነው።

በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉትን ሀገራዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አራቱን ምሰሶዎች የሚሸፍን እና የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን ሁለንተናዊ ዓላማ የሚያንፀባርቅ መሆኑ ተፈላጊ ነው። የተለያዩ ቡድኖችን እና ሴክተሮችን ልዩ ልዩ ፍላጎቶችን፣ ቅድሚያዎችን እና አመለካከቶችን ለመያዝ ይችል ዘንድ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ከተለያዩ የመንግስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የሲቪል ማህበራት ተዋናዮች እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ማለትም እንደ አካዳሚው፣ ሚዲያ እና አጋር ሀገራት ጋር በመሆን መዘጋጀት ይኖርበታል።የተሳካ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ከሌሎች ነባር ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች ጋር የተያያዘ መሆን ያስፈልጋዋል፣ ለምሳሌ በሠላም፣ በጸጥታ፣ በሥርዓተ-ጾታ እኩልነት እና በልማት ዙሪያ። መርሃ ግብሩ ሁለቱንም የሀገር እና የውጭ ፖሊሲ አመለካከቶችን እና የቅድሚያ ጉዳዮችን ሊያካትት ይችላል።አፈጻጸማቸውን መከታተል የሚቻል የሆኑ የተለያዩ ተዋናዮችን ተግባር በአንድ ማዕቀፍ ውስጥ ማቀናጀት ስለሚያስችል የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር መዘጋጀት በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ዙሪያ የተሻሻለ ክትትልንና ግምገማን እንዲሁም የተጠናከረ የተጠያቂነት አሰራርን

[1] See, e.g.: UN Women. Facts and figures: Women, peace, and security (webpage): https://www.unwomen.org/en/what-we-do/peace-and-security/facts-and-figures; and Council on Foreign Relations. Women's Participation in Peace Processes (webpage): https://www.cfr.org/womens-participation-in-peace-processes/.

[2] United Nations Security Council Resolutions 1820 (2008); 1888 (2008); 1889 (2009); 1960 (2010); 2106 (2013); 2122 (2013); 2242 (2015); 2467 (2019); and 2493 (2019).

[3] Presidential Statements S/PRST/2002/32; S/PRST/2004/40; and S/PRST/2005/52.

ይፈጥራል።

በአሁኑ ወቅት 103 አባል ሀገራት የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ተቀብለዋል፤ ከእነዚህም ውስጥ 30ዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ናቸው። ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች በግጭት ውስጥ (ለምሳሌ በደቡብ ሱዳን እና በየመን) እና ከግጭት በኋላ ባሉ ሁኔታዎች (ለምሳሌ ላይቤሪያ እና ኔፓል) እንዲሁም ለረዥም ጊዜ ከፍተኛ ግጭት ባላጋጠማቸው አገሮች (ለምሳሌ ዮርዳኖስ እና ናሚቢያ) ተቀባይነትን አግኝተው ጥቅም ላይ ውለዋል። ከሀገራዊ ጉዳዮች በተጨማሪ በአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት እና በሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ በአፍሪካ የተቀመጡትን መሳሪያዎች እና ቃል ኪዳኖች ትግበራን የመከታተል ዓላማን የሚያገለግሉ እንደ የአፍሪካ ህብረት አህጉራዊ ውጤቶች ማዕቀፍ (Continental Results Framework of the African Union) ያሉ አህጉራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች እና ማዕቀፎች አሉ።

## 2. የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት ሂደት

የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ብዙ ተደራራቢ ተግባራት ሊኖሩት ይችላል፤ በሀገሪቱ ያሉ የሴቶችን ደረጃ ለማሻሻል፣ የሴቶችን ተሳትፎ እና ሰላምና ደህንነትን የተመለከቱ አለም አቀፍ ህጎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማውረድ፣ ከሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ጋር የተያያዙ ስምምነቶችን ወደ አንድ ማዕቀፍ ለማምጣት፣ የሀገሪቱን ግጭት የመከላከል አቅም ለማሳደግ እና ለውጭ ፖሊሲ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ተደራሽ የማድረጊያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት ሂደት በእያንዳንዱ ሀገር የተለያየ ነው፣ ነገር ግን ሂደቱ በዋናነት አንድ መንግስት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶችን እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ለይተው ማወቅ፣ ፍላጎቶቹንም ለማሳካት እርምጃዎችን ማቀድ እና በእነርሱ ላይ ለመስራት ቃል መግባት ማለት ነው። ይህ ምዕራፍ የዚህን ሂደት ዋና ዋና ደረጃዎች ይመለከታል።

የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ለማዘጋጀት የመጀመሪያው ደረጃ ከብዙ ምንጮች ሊመጣ ይችላል። ለምሳሌ **ደቡብ ሱዳን** ውስጥ፣ አገሪቱ ነጻነት ካገኘች በኋላ፣ መንግስት በግጭቶች ወቅት የሴቶችና ልጃገረዶችን ሁኔታ ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ተመልክቷል። ስለሆነም መንግስት እንደ ብሔራዊ የሥርዓተ-ፆታ ፖሊሲ[4] ያሉ ሌሎች አገራዊ ፖሊሲዎችንና ዕቅዶችን ለመደገፍ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅትን ጀመሯል። **በናሚቢያ** ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የተዘጋጀው ሴቶችን በሰላምና ጸጥታ ሂደቶች ውስጥ ለማካተት እና ሁሉንም በአንድ ማዕቀፍ[5] ውስጥ ለማስገባት ቀደም ብሎ የተሰራውን ስራ ለማፋጠን ነው። የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ለማዘጋጀት ቁርጠኝነትን ለመፍጠር የሲቪል ማህበረሰቡ ተሟጋችነት ትልቅ አስተዋፅኦ ካደረገበት **ከካሜሩን** ለየት ያለ ምሳሌ ይመጣል።[6]

የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት የተለያዩ ተዋናዮችን የሚያስተዋውቅ ሂደት ሊሆን ይችላል፣ ለምሳሌ የመንግስት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ከሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ጋር። የመርሃ ግብር ዝግጅቱ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ እውቀትን ይጨምራል፣ በዚህም የትስስር መረቦችን እና መተማመንን፣ ለምሳሌ በመንግስት እና በሲቪል ማህበረሰብ መካከል ይፈጥራል። የተለያዩ ቡድኖች እና ተዋናዮች ልምዶችን ለመለዋወጥ በአንድ ላይ ሲገናኙ ሂደቱ በራሱ የግጭት አፈታት ወይም የእርቅ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ስለዚህ በሴቶች፣ ሰላምና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት ዕቅዱ ብቸኛ ውጤቱ ያልሆነለት ሂደት ተደርጎ መታየት አለበት። **በደቡብ አፍሪካ** ውስጥ የነበረውም ሁኔታ ይህ ነበር፣ ሂደቱ በጣም ረጅም ጊዜ የፈጀበት ነገር ግን የተሰጠው ጊዜ የተለያዩ ተዋናዮች በርዕሰ-ጉዳዩ ዙሪያ ስምምነት እና የጋራ መግባባት እንዲፈጥሩ በማድረጉ ምክንያት መጨረሻ ላይ ሂደቱ በአዎንታዊ መልክ ታይቷል።[7]

የተሳካ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደት ቁልፍ ባህሪያት የሚከተሉትን ያካትታሉ:-[8, 9]

- የበርካታ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ወይም የመንግስት ኤጀንሲዎች ፖለቲካዊ ፍላጎት እና ሰፊ ተሳትፎ

[4] Republic of South Sudan (2015) *South Sudan National Action Plan 2015-2020 on UNSCR 1325 on Women, Peace and Security and Related Resolutions:* http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2020/12/SS-NAP-1325.pdf
[5] Republic of Namibia (2019) *Namibia National Action Plan on Women, Peace and Security:* http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2020/12/Namibia-NAP-2019-2024.pdf
[6] Women's International League of Peace and Freedom. *WILPF welcomes the adoption of Cameroon's UNSCR 1325 NAP* (webpage): http://www.peacewomen.org/node/101027
[7] Republic of South Africa (2020) *National Action Plan on Women, Peace and Security – 2020 to 2025 South Africa*: http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2021/06/sa_national_action_plan_women_peace_security_2020-2025.pdf
[8] Republic of South Africa (2020) *National Action Plan on Women, Peace and Security – 2020 to 2025 South Africa*: http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2021/06/sa_national_action_plan_women_peace_security_2020-2025.pdf
[9] UN Women (2012) *Women and Peace and Security: Guidelines for National Implementation:* https://www.unwomen.org/-/media/headquarters/attachments/sections/library/publications/2012/10/wpssourcebook-02b-planonwomenpeacesecurity-en.pdf?la=en&vs=1154

- በሂደቱ ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎ፤ የሴቶች ድምጾች መካተት
- የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ተግባራት
- በመሪው ሚኒስቴር ወይም በኤጀንሲው ጠንካራ አመራር እና ውጤታማ ቅንጅት
- የየአውዱን ቅድሚያዎች እና ተግባራትን መለየት
- ስልታዊ የክትትል እና የግምገማ ማዕቀፎች በጊዜ ከተገደቡ ጠቋሚዎች ጋር
- ለትግበራ የሚሆን በቂ የሀብት ድልድል
- ተለዋዋጭ የጸጥታ ሁኔታዎችን ጨምሮ ብቅ የሚሉ/የሚከሰቱ ሁኔታዎችን ለመላመድ የሚያስችል ተለዋዋጭነት

### ዋና ሚኒስቴር መ/ቤቶችን መለየት እና ግብረ-ኃይል ማቋቋም

ከአለም አቀፍ ተሞክሮዎች በመነሳት ብዙ አመለካከቶችን ለማካተት እና ዕቅዱ ከሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ አቀራረብ እንዲኖር ስለሚያስችል፣ በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደት በርካታ ሚኒስቴር መ/ቤቶች እና የመንግስት ኤጀንሲዎች ሲሳተፉ የተሻሉ ውጤቶችን ያስገኛል። በተጨማሪም መሪ የመንግስት የሚኒስቴር መ/ቤት ወይም ኤጀንሲ ምርጫ አስፈላጊ እርምጃ ነው። በብዙ አገሮች የሴቶችና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን የሚመለከተው ሚኒስቴር እንደ መሪ ሆኖ አገልግሏል፣ ነገር ግን ሌሎች አማራጭ መንገዶችም አሉ። ለምሳሌ እንደ መከላከያ ወይም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያለን አስፈፃሚ ሚኒስቴር በመሪነት እና በአስተባባሪነት ሚና አድርጎ ማንቀሳቀስ የዕቅዱን ለሰላምና ጸጥታ ጉዳዮች አስፈላጊነት በተመለከተ ምልክት ስለሚያሳይ ዕቅዱን በሁሉም የሚመለከታቸው ሴክተሮች እንዲካተት ለማድረግ ይረዳል። **ላይቤሪያን**[10] በተመለከተ፣በሌላ በኩል፣ የፕሬዚዳንት ኤለን ጆንሰን-ሰርሊፍ ለብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር መፈጠር የማያቋርጥ እና ግልጽ ድጋፍ መስጠት በአገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ ፍላጎትን ፈጠሯል።

**በሞዛምቢክ** የሥርዓተ-ፆታ፣ የህጻናት እና ማህበራዊ ጥበቃ ሚኒስቴር እንደ መሪ ኤጀንሲ ሆኖ አገልግሏል። **ካሜሩን** ውስጥ መሪ ኤጀንሲው እና የሂደቱ አነሳሽ የሴቶች ማብቃት እና የቤተሰብ ሚኒስቴር የነበረ ሲሆን **በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ** ውስጥ ደግሞ የሥርዓተ-ፆታ፣ ቤተሰብ እና ህፃናት ሚኒስቴር ተመሳሳይ ሚና ነበረው። መሪ ሚኒስቴር ወይም ኤጀንሲ ከመሾም በተጨማሪ፣ ብዙ ሀገራት በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ውስጥ በሚሳተፉ የተለያዩ ተዋናዮች መካከል ያለውን ሥራ የሚያስተባብር እና የሚመራ የሥራ ቡድን፣ የአመራር ኮሚቴ ወይም ግብረ-ኃይል አቋቁመዋል። በእነዚህ ተግባራት ውስጥ የተወከሉት ሃይሎች፣ እንደ ሀገሩ እና እንደ አውዱ፣ የተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ፓርላማ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የጸጥታ ሴክተር ኤጀንሲዎች፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲዎች እንዲሁም አጋር እና ለጋሽ ሀገራት ናቸው። የእነዚህ ግብረ-ኃይሎች ሚና የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደትን መቆጣጠር፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ ድምጾችን ማሰባሰብ እና የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ከሌሎች አለም አቀፍ እና ሀገራዊ ዕቅዶች፣ ፖሊሲዎች እና ቃል ኪዳኖች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

**በሴራሊዮን** የመንግስት-የሲቪል ማህበረሰብ ግብረ-ኃይል 35 የመንግስት፣ የሲቪል ማህበረሰብ እና የአካባቢ ድርጅቶችን ያቀፈ ነበር። ግብረ-ኃይሉ በማህበራዊ ደህንነት፣ ስርዓተ-ፆታ እና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ሰብሳቢነት የተመራ ነበር። **በናሚቢያ፣** የመከላከያ ሚኒስቴር በሰብሳቢነት፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እና የሕፃናት ደህንነት ሚኒስቴር፣ የዓለም አቀፍ ግንኙነት እና ትብብር ሚኒስቴር እና የተባበሩት መንግስታት የቴክኒክ አማካሪዎችን ያቀፈ ብሔራዊ የተግባር ቡድን ለብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ኃላፊነት ነበረው።

በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ትግበራ ሂደት ውስጥ የመረጃ አሰባሰብ እና የማርቀቅ ሂደቱን እንዲሁም የግብረ-ኃይሉን ወይም የአመራር ኮሚቴውን ስራ ለማሳለጥ ባለሙያዎችን እና ቴክኒካል አማካሪዎችን መጠቀም የተለመደ ነው። ለምሳሌ **በናሚቢያ** ሂደቱን የሚያሳልጥ እና የሚመራ ባለሙያ የተሾመ ሲሆን፣ ከዩኤን ውሜን የደቡብ አፍሪካ የብዙ ሀገር ቢሮ (UN Women South Africa Multi Country Office (SAMCO)) አንድ የቴክኒክ አማካሪ ለሂደቱ ድጋፍ ሰጥቷል። **በደቡብ ሱዳን** ሁለት አማካሪዎች (አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ) የዕቅዱን ዝግጅት እና ጥንቅር አሳልጠዋል ።

### ፍላጎቶችን ለመለየት ጥናቶችን እና ምዘናዎችን ማካሄድ

የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታን በተመለከተ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደትን ለመደገፍ ጥሩ ልምድ የሚሆነው የሥርዓተ-ፆታ የግምገማ ወይም የመነሻ ጥናት ማድረግ ነው። ከሌሎች ሃገራት በተጨማሪ እንደ **ቡሩንዲ፣ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ ደቡብ ሱዳን** እና **ሩዋንዳ** ባሉ ሀገራት ውስጥ የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች አደረጃጀት ከመፈጠሩ በፊት በማህበረሰብ ደረጃ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመጠቀም የመነሻ ጥናቶች ተካሂደዋል። **በካሜሩን** የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት (የሴቶች ዓለም አቀፍ የሰላም እና የነፃነት ሊግ (WILPF) ካሜሩን) በሴቶች ማብቃት እና ቤተሰብ ሚኒስቴር እና በተባበሩት መንግስታት የሴቶች ቴክኒካዊ ቁጥጥር ስር ብሔራዊ የመነሻ ጥናት አካሂዷል። እንደነዚህ ያሉ ጥናቶች በብሔራዊ ወይም በአካባቢ አውድ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ቅድሚያዎች ለመለየት ስለሚረዱ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እና ፍላጎቶችን ለመለየት

[10] Republic of Liberia (2009) *The Liberia National Action Plan for the implementation of the United Nations Resolution 1325*: http://peacewomen.org/sites/default/files/liberia_nationalactionplanmarch2009.pdf

አስፈላጊ መሳሪያዎች ነበሩ። ይህንን መረጃ በመጠቀም ግቦችን እና ዒላማዎችንም ማዘጋጀት ይችላል፣ እና መረጃው በተወሰኑ አመልካቾች ላይ በመመስረት እንደ የእድገት ለውጥን መከታተል የሚቻልበት የመነሻ ጥናት ሆኖ ያገለግላል። በአገር አቀፍ የጸጥታ ኃይሎች ውስጥ ያሉ የሴቶች ቁጥር፣ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች መስፋፋት፣ ቀደም ሲል የነበሩት የግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶች፣ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ሴቶችና ወንዶች የሚገጥሟቸው የጸጥታ ሥጋቶች፣ በአገር ውስጥና በአካባቢው ውስጥ በብሄራዊ የሰላም ግንባታ እና እርቅ ጥረቶች ውስጥ የሚሳተፉ የሴቶች ቁጥር ከርዕሰ-ጉዳዮች መካከል ለአብነት ይጠቀሳሉ።

ተቋማዊ ኦዲቶች የወቅቱን ማሳያ ሁኔታ ማለትም እንደ ከሴቶች ጋር የተያያዙ ህጎችን እና ደንቦችን፣ የሰላም እና የጸጥታ አጀንዳን እና ነባር የገንዘብ እና የሰው ሃብታትን (resources) የመሳሰሉትን ሊያሳዩ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ጥናቶች እና ግምገማዎች በሀገሪቱ ውስጥ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ እየሰሩ ያሉ ተዋናዮችን እና የእነርሱንም በሥራቸው ቅድሚያ የሚሰጡዋቸውን ለመለየት እና በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ስላላቸው ነባራዊ መረዳት ግንዛቤዎችን ለማግኘት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላል።

የመነሻ ጥናቶች እና ግምገማዎች በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ በአራቱም ዘርፎች (ምሰሶዎች) ያለውን ሁኔታ እና ነባራዊ ፍላጎቶችን ለመለየት ያለሙ መሆን አለባቸው። የሰላም እና የግጭት ጉዳዮች መነሻቸው በሰፊው ህብረተሰብ ውስጥ እና እንዲሁም ከግጭት-ዞኖች ውጭ የሆኑ ክስተቶች መሆናቸውን በመገንዘብ መቅረብ አስፈላጊ ነው።[11]

## ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክሮች እና የሲቪል ማህበረሰብን ተሳትፎ ማረጋገጥ

አጠቃላይ እና ተግባራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በመንግስት ተቋማት፣ በሲቪል ማህበረሰብ እና እንደ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች፣ አካዳሚ እና አጋር ሀገራት በመሳሰሉ ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል የዕቅዱን ውክልና፣ ተሳትፎ እና ባለቤትነት ለማረጋገጥ ሰፊ እና አንዳንዴም ረጅም የምክክር ሂደትን ይጠይቃል። በዕቅዱ ዝግጅት ውስጥ ከፍ ያሉ ደረጃዎች ያሉት ተሳትፎ ከፍ ያለ ባለቤትነት እና ለተግባራዊነቱ ቁርጠኝነት እንዲኖር ያስችላል።

**የካሜሩንን** ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ለማዘጋጀት የሴቶች ማብቃት እና ቤተሰብ ሚኒስቴር በግንባር ቀደምትነት የሰራ ሲሆን ሌሎች አካላትም በሂደቱ ውስጥ ተሳትፈዋል። በእነዚህም አካላት ውስጥ የመንግስት እና የፓርላማ አባላት፣ ያልተማከሉ የክልል ማህበረሰቦች ተወካዮች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና አለም አቀፍ ድርጅቶች እና ሌሎችም ይገኙበታል። **በኔፓል** የክልል ምክክሮች ተሳታፊዎች ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት እስከ በግጭት የተጎዱ ህፃናት እና ከሀገር አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እስከ የአካባቢ የሴቶች ቡድኖች ድረስ የተገኙበት ነበር። የባለድርሻ አካላት ምክክሮች በመንግስት ወይም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሊመሩ ይችላል። ዓላማቸውም መረጃ መስጠት፣ ውይይቶችን ማድረግ እና ከሰፊ የህዝብ መሰረት ግብአቶችን ባሳተፈ መልኩ ማሰባሰብ ነው። የተሳታፊዎች ውይይቶች እና አስተያየቶች የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን ለማዘጋጀት ትርጉም ባለው መልኩ ሊመሩበት በሚገባ መንገድና ጊዜ ሊዘጋጁ ይገባል።[12] ግብአት ለማሰባሰብና የረቂቁን ሂደት ለመምራት ከሚደረጉ ምክክሮች በተጨማሪ የማረጋገጫ አውደ ጥናቶች የመጨረሻው ረቂቅ በይፋ ከመጽደቁ በፊት ለባለድርሻ አካላት ለማቅረብ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

የሲቪል ማህበረሰብ መንግስታትን ተጠያቂ ለማድረግ ወሳኝ ሚና አለው፣ ለምሳሌ በአፈፃፀሙ ላይ ግምገማ እና ክትትል በማድረግ። የሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች የመንግስትን እውቀትና ሀሳቦችን የሚደግፉ እውቀትና ሀሳቦችን የያዙ በመሆናቸው የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎ ለበለጠ ውጤታማ እና ሁሉን-አቀፍ ዕቅድ መሰረት ይጥላል። ለምሳሌ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የሴቶች ቡድኖች ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ለመድረስ አስቸጋሪ በሆኑ አካባቢዎች ወይም የተፈናቀሉ ህዝቦችን በማሳተፍ ለፍላጎቶቻቸው የበለጠ ምላሽ የሚሰጥ ዕቅድ በማውጣት ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ስለዚህ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ለማዘጋጀት እነርሱን በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ነው።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የሴቶች ኔትዎርኮች በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ላይ በተለያየ መንገድ ሊሳተፉ ይችላሉ። የላቀ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የሲቪል ማህበራት ከሂደቱ መጀመሪያ ጀምሮ መሳተፍ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፣ **በፊሊፒንስ፣** የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር እድገት ሂደትን ከመጀመሪያው ጀምሮ ለይቶ ያስቀመጠው የመሰናዶ ኮሚቴ አባላት ነበሩ።[13] ከላይ እንደተገለጸው፣ በብዙ ሀገራት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሂደቱን የሚያስተባብሩ የብሔራዊ ግብረ-ኃይሎች አባላት ናቸው። **በሴራሊዮን** የሲቪል ማህበረሰብ ተሟጋችነት በሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች የተጀመረ በመሆኑ ምክንያት የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ በጣም መሰረታዊ ነበር። በተጨማሪም በመንግስት-ሲቪል የማህበረሰብ ግብረ-ኃይል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ተዋናዮች ሰፊ ውክልና የድርጊት መርሃ ግብሩን

[11] UN Women (2012) *Women and Peace and Security: Guidelines for National Implementation:* https://www.unwomen.org/-/media/headquarters/attachments/sections/library/publications/2012/10/wpssourcebook-02b-planonwomenpeacesecurity-en.pdf?la=en&vs=1154

[12] Women's International League for Peace and Freedom (2014) *Leveraging UNSCR 1325 National Action Plans for Local Change. Civil Society Opportunities in the MENA Region*: https://wilpf.org/wp-content/uploads/2015/09/Leveraging-UNSCR-1325-National-Action-Plans-for-Local-Change.pdf

[13] Steinberg et al. (2015) *Implementation of UN Security Council Resolution 1325 in Israel. Implementing and Monitoring National Action Plans: Strategies of Women's Organizations*: https://il.boell.org/sites/default/files/nap-_strategies_of_womens_organizations.pdf

በሀገሪቱ ውስጥ ካሉ የተለያዩ ሁኔታዎች ጋር ለማስማማት ጠንካራ አካባቢያዊ ፍላጎት እንዲኖር አመቻችቷል።[14]

በምክክሮች እና በግብረ-ኃይሎች ውስጥ መሳተፍ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ውስጥ ለማካተት መደበኛ መንገዶች ናቸው። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ግብዓታቸውን መደበኛ ባልሆኑ መንገዶች ለምሳሌ የጥብቅና ዘመቻዎችን እና ሪፖርቶችን በማዘጋጀት መስጠት ይችላሉ። ለምሳሌ **የካሜሩን** እና **የኡጋንዳ** የሴቶች ቡድኖች የሴቶች፣ ሰላም እና የጸጥታ አጀንዳ ዕውቀትን ለመጨመር እና ለብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ለመደገፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን አዘጋጅተዋል።

የሲቪል ማህበረሰቡ ብሄራዊ ኔትዎርኮችን በፈጠረበት እንደ **ፊሊፒንስ፣ ላይቤሪያ** እና **አየርላንድ** ሁኔታዎች በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደት ላይ የሲቪል ማህበረሰቡን ተጽእኖ ከፍ ለማድረግ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ብዙውን ጊዜ ጥምረት ይፈጥራሉ። ይህም በሂደቱ ውስጥ የተለያዩ የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖችን ተሳትፎ የሚደግፍ ሲሆን በፖሊሲ እና በአሰራር መካከል ያለውን ልዩነትም ለማስተካከል ይረዳል።[15,16] ከሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት በተጨማሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን በመተግበር ላይ ይፋዊ ሚናዎች ሊሰጧቸው ይችላል። **በኔፓል** እና **በሴራሊዮን** የሲቪል ማህበራት ለአካባቢያዊ ትግበራ ኃላፊነቶችን ሰይመዋል።[17] እንደ **ኔዘርላንድስ** ባሉ አንዳንድ ሀገራት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ተባባሪ ፈራሚዎችም ነበሩ።[18]

**ለትግበራ፣ ለክትትልና ለግምገማ አወቃቀሮችን ማዘጋጀት**
ፍላጎቶችን ከመለየት እና ተግባራትን ከመዘርዘር በተጨማሪ፣ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት አስፈላጊው ሁኔታ ወይም ገጽታ የሚመለከታቸውን አካላት ለአፈፃፀም የሚኖራቸውን ኃላፊነት መወሰን እንዲሁም ለክትትልና ለግምገማ ግልጽ የሆነ መዋቅር ማስቀመጥ ነው። የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩ ዝግጅትን መከታተል እንዲቻል እና ተጠያቂነትን ለማስፈን አመላካቾችን ማካተት አለበት። በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ወቅት የተለዩ እና ተጨባጭ ውጤቶችን እና አመላካቾችን በተመለከተ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ወይም አፈፃፀሙን በሚመለከት የኃላፊነት ክፍፍሉ ግልጽ ካልሆነ፣ የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር መፍትሄ ለመስጠት የወሰናቸውን ጉዳዮች ለመፍታት የትግበራው ምዕራፍ ከአጥጋቢ ያነሰ ወይም ውጤታማ ላይሆን ይችላል።[19] የተባበሩት መንግስታት በብሔራዊ አውድ ላይ በመመስረት በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች ሊተገበሩ የሚችሉ አመላካቾችን[20] ዝርዝር አዘጋጅቷል።

**በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ**[21]፣ የሁለተኛው ትውልድ የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ትግበራ የልዩ ባለ ሶስት ደረጃ አስተባባሪ ኮሚቴ (Steering Committee) መዋቅርን ማለትም የብሄራዊ፣ የግዛት እና የአካባቢ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ለመፍጠር የተነደፈ ነበር፤ እያንዳንዳቸውም የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ተግባራዊ ለማድረግ የተለየ ተግባር ተሰጥቷቸዋል። ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴው ፖሊሲና ብሔራዊ ሂደቱን ለማዘጋጀት ኃላፊነትን ወስዷል። ኮሚቴው የተለያዩ የሚኒስቴር መ/ቤቶች ተወካዮችን፣ ፓርላማን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ የሃይማኖትና የባህል ባለሥልጣናትን፣ የብሔራዊ ጸጥታ ዘርፍ ተዋናዮችን እና የልማት አጋሮችን ያጠቃልላል። የግዛት እና አካባባዊ አስተባባሪ ከሚቴዎች ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ከራሳቸው አካባባያዊ አውዶች ጋር የማዋሀድ፣ የመተግበር እና የመገምገም ኃላፊነት አለባቸው።

**የካሜሩን**[22] የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ትግበራ ማዕቀፍ ሶስት አካላትን ያቀፈ ነው፣ እነዚህም የሙከራ እና ማስተዋወቅ ኮሚቴ፤ የ1325 ብሄራዊ ቴክኒካል አስተባባሪ፤ የክልል፣ የክፍል እና

[14] Nairobi Symposium: Maximizing Impact of Women, Peace, and Security Policies in Africa was organized by the Institute for Inclusive Security, University of Nairobi and Cordaid in July 2014. Conference report: http://www.inclusivesecurity.org/wp-content/uploads/2015/02/Nairobi_Symposium_Conf_Report.pdf

[15] Women's International League for Peace and Freedom (2014) *Leveraging UNSCR 1325 National Action Plans for Local Change. Civil Society Opportunities in the MENA Region*: https://wilpf.org/wp-content/uploads/2015/09/Leveraging-UNSCR-1325-National-Action-Plans-for-Local-Change.pdf

[16] Steinberg et al. (2015) *Implementation of UN Security Council Resolution 1325 in Israel. Implementing and Monitoring National Action Plans: Strategies of Women's Organizations*: https://il.boell.org/sites/default/files/nap-_strategies_of_womens_organizations.pdf

[17] Women's International League for Peace and Freedom (2014) *Leveraging UNSCR 1325 National Action Plans for Local Change. Civil Society Opportunities in the MENA Region*: https://wilpf.org/wp-content/uploads/2015/09/Leveraging-UNSCR-1325-National-Action-Plans-for-Local-Change.pdf

[18] UN Women (2012) *Women and Peace and Security: Guidelines for National Implementation:* https://www.unwomen.org/-/media/headquarters/attachments/sections/library/publications/2012/10/wpssourcebook-02b-planonwomenpeacesecurity-en.pdf?la=en&vs=1154

[19] ibid.

[20] 20Report of the Secretary General S/2010/498, page 33: https://www.securitycouncilreport.org/atf/cf/%7B65BFCF9B-6D27-4E9C-8CD3-CF6E4FF96FF9%7D/WPS%20S%202010%20498.pdf

[21] The Democratic Republic of the Congo: *National Action Plan* (Unofficial translation, funded by ARC DP160100212 [CI Shepherd]): http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2020/12/DRC-NAP-2019.pdf

[22] Republic of Cameroon (2017) *National Action Plan for the 1325 Resolution and Companion Resolutions of the United Nations Security Council on Women, Peace and Security (2018-2020):* http://pwnap1.tetra.in/wp-content/uploads/2020/10/Cameroon-2018-English.pdf

ንዑስ-ክፍል መምሪያዎች ናቸው። የሙከራ እና ማስተዋወቅ ኮሚቴ (the piloting and orientation committee) በሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት ዋና ጸሃፊ ስልጣን ስር የተደረገ ሲሆን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ዋና ጸሃፊ የሚታገዝ ነው። ኮሚቴው የሪፐብሊኩን ፕሬዝዳንት፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትን፣ ሴኔትን፣ ብሔራዊ ምክር ቤትን፣ የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶችን፣ የጸጥታ ዘርፍ ተዋናዮችን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን እና የግሉ ሴክተር ተወካዮችን ጨምሮ 20 አባላትን በመያዝ የተቋቋመ ነው። ኮሚቴው የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አፈፃፀም አጠቃላይ መመሪያዎችን ይወስናል እንዲሁም የድርጊት መርሃ ግብሩን አፈፃፀም ይከታተላል። ብሔራዊ የቴክኒክ አስተባባሪ ተጠሪነቱ ለሴቶች ማብቃት እና ቤተሰብ ሚኒስቴር ሆኖ ክትትል እና አፈፃፀሙን በመገምገም ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ሃላፊነት አለበት። የክልል፣ የክፍል እና የንዑስ ክፍል ዲፓርትመንቶች ተጠሪነታቸው በቅደም ተከተል ለክልል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ ለከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እና ለክፍል ኃላፊዎች ሆኖ እና አፈጻጸሙን በብቃት በአካባቢዎቻቸው በመከታተል ለሀገር አቀፍ ደረጃ መረጃ ይሰጣሉ።

**በሞዛምቢክ** የክትትልና ግምገማ ኮሚቴ ተቋቁሟል። ኮሚቴው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናዮችን እና ከሁለቱም ከመንግስት እና ከሲቪል ማህበረሰቡ አንፃር ያሉ እይታዎችን ሪፖርት ያደርጋል።[23] **በሴራሊዮን**[24] የማህበራዊ ደህንነት፣ የስርዓተ-ፆታ እና የህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር የዕቅዱ አጠቃላይ ክትትል አድራጊ እና ገምጋሚ ነው። ሂደቱ በሦስት ደረጃዎች ይከናወናል፡-ብሔራዊ፣ ክልላዊ እና የዲስትሪክት አስተባባሪ ኮሚቴዎች የዕቅድ አፈፃፀም መረጃን ሰብስበው ይተነትናሉ። የክልል እና የዲስትሪክት አስተባባሪ ኮሚቴዎች መረጃን ለብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ያሳውቃሉ፤ ኮሚቴውም ለመንግስት፣ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት አካላት እና ለለጋሽ ድርጅቶች ያሳውቃል። በብዙ ሀገራት፣ ለምሳሌ **በሴራሊዮን** እና **በላይቤሪያ** ባሉ ሁኔታዎች፣ የበለጠ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮችን በሃገር አቀፍ እና በአከባቢ ደረጃ አስተባባሪ ኮሚቴዎች እና ግብረ-ኃይሎች ውስጥ በማካተት የሲቪል ማህበረሰቡ የዕቅዱን አፈፃፀም በመከታተል ላይ መደበኛ ሚና ተሰጥቶታል።

### በቂ የሀብት (Resource) ድልድልን ማረጋገጥ

ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ስኬታማ እንዲሆን እና ለውጥ-አምጪ የድርጊት መርሃ ግብር እንዲሆን ከፖለቲካዊ ፍላጎት በተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልገዋል።ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ለተግባራቱ ማስፈጸሚያ እንዲሁም ለማስተባበር፣ ለክትትል እና ለግምገማ የሚሆኑ በቂ ሃብታት (resources) ያሉት በጀት ማካተት ይኖርበታል፣ ይህ ደግሞ ከብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደት ጀምሮ ሊታሰብበት ይገባል። ለትግበራው የሃብታት (resources) እጥረት በብዙ አገሮች ቀጣይነት ያለው ችግር ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች መካከል 36 በመቶው ብቻ የተመደበ በጀትን ያካትታሉ።[25]ይህ ጉዳይ በጋራ ለመስራት ተነድፎ እና ቁርጠኝነት ታይቶበት የነበረ ዕቅድ ተግባራዊ ሳይሆን መቅረቱ ሲታይ በዕቅዱ አፈጻጸም ላይ ትልቅ እንቅፋት ከመፍጠሩም ባለፈ ጥርጣሬን በመፍጠር በባለድርሻ አካላት ዘንድ እምነትን የሚሸረሽር ነው።

የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ተግባራት በመንግስት የበጀት አወጣጥ ሂደት ውስጥ መካተት ያለባቸው ሲሆን፣ ተስማሚ ከሆነ የውጭ የገንዘብ ምንጮችም ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። ለምሳሌ፣ በናሚቢያ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ስራዎች ለበጀት ማዕቀፎች እንደ ጭማሪዎች ሆነው የተፈጠሩ አልነበሩም፣ ነገር ግን በመንግስት በጀት ውስጥ የተካተቱ ነበሩ። ሆኖም ግን፣ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በሚፃፍበት ጊዜ ሁሉንም የዕቅዱን ስራዎች ለመሸፈን የመንግስት ሃብታት (resources) በቂ እንዳልነበሩ በመገንዘብ ከልማት አጋሮችና ከግሉ ሴክተር የሚደረጉ የገንዘብ ድጋፎች የሃብት (resource) ክፍተቱን ለመቅረፍ እንደሚያስፈልጉ ታውቋል።[26] የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የወጪ እና የበጀት አውደ ጥናት ለሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ተጨባጭ በጀት ለመፍጠር ጠቃሚ መሳሪያ ሊሆን ይችላል።[27]

### የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የስራ ሂደት መዘርዝር ምሳሌዎች

**በናሚቢያ**[28] የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ለማዘጋጀት መደበኛ ቃል ኪዳን በሚያዝያ 2016 ተገብቷል። በመከላከያ ሚኒስቴር የሚመራ ብሔራዊ የተግባር

[23] Republic of Mozambique (2018) *National Action Plan on Women, Peace and Security (2018-2022):* http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2020/12/Mozambique-NAP-2018-2022.pdf
[24] Republic of Sierra Leone (2010) *The Sierra Leone Action Plan for the Full Implementation of the United Nations Security Council Resolutions 1325 (2000) and 1820 (2008): http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2020/12/sierra_leone_nap.pdf*
[25] Women's International League for Peace and Freedom. *1325 National Action Plans (NAPs)* (webpage): http://1325naps.peacewomen.org/

[26] Republic of Namibia (2019) *Namibia National Action Plan on Women, Peace and Security:* http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2020/12/Namibia-NAP-2019-2024.pdf
[27] Global Network of Women Peacebuilders (2017*) No Money, No NAP. Manual for Costing and Budgeting National Action Plans on UNSCR 1325*: https://gnwp.org/wp-content/uploads/GNWPCostingBudgetingManual_Eng_4web.pdf
[28] Republic of Namibia (2019) *Namibia National Action Plan on Women, Peace and Security:* http://1325naps.peacewomen.org/wp-content/uploads/2020/12/Namibia-NAP-2019-2024.pdf

ቡድን ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን የማዘጋጀት ኃላፊነትን ወስዷል ። ከሲቪል ማህበረሰብ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ለምሳሌ ከሴቶች ድርጅቶች፣ ከባህላዊ ባለስልጣናት፣ ከጸጥታ ሴክተር ተቋማት እና ከአለም አቀፍ አጋሮች ጋር ምክክሮች ተካሂደዋል። ምክክሮቹ ለሁለት አመታት ያህል የዘለቁ ነበር። በሂደቱ ውስጥ ባሉ ወቅታዊ ሁኔታዎች እና ፍላጎቶች ላይ የዴስክ ዳሰሳ ተካሄዷል።ብሄራዊ ግብረ ቡድኑ በሂደቱ ውስጥ በርካታ ስብሰባዎችን ያካሄደ ሲሆን ለባለድርሻ አካላት የመጨረሻው የማረጋገጫ ስብሰባ በሐምሌ 2018 (እ.ኤ.አ.) ተካሄዷል። ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩ በየካቲት 2019 (እ.ኤ.አ.) በካቢኔ ተቀባይነት አግኝቷል።

**በደቡብ ሱዳን** ሂደቱ የተጀመረው በስርዓተ-ፆታ፣ ህጻናት እና ማህበራዊ ደህንነት ሚኒስቴር በ2011 (እ.ኤ.አ.) ነው። ሚኒስቴሩ ሁለት መሰረታዊ ጥናቶችን አድርጓል። የመንግስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ኮሚሽኖች፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኤጀንሲዎች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ያቀፈ ብሄራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን፣ በ2013 (እ.ኤ.አ.) ለኮሚቴው የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ እና የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት ሂደት ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖረው የምክክር አውደ ጥናት ተዘጋጅቷል። የዕቅዱ ዝግጅት እና ማጠናቀር ከአስተባባሪ ኮሚቴው የቴክኒክ ሥራ ቡድን በተገኘ ምክር ለሁለት አማካሪዎች ተሰጥቷል።

ከመንግስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲዎች፣ ከልማት አጋሮች እና ከሲቪል ማህበራት ለተውጣጡ ተወካዮች ግብዓት ለማሰባሰብ እና በተለያዩ ተዋናዮች ውስጥ ግንዛቤ ለማስጨበጥ እና ትስስሮችን ለመፍጠር ሀገር-አቀፍ የምክክር አውደ ጥናት ተካሄዷል። በተጨማሪም በ2013 (እ.ኤ.አ.) በአማካሪዎች እና በአስተባባሪ ኮሚቴው አባላት የተመቻቹ ምክክሮች በአስሩም ስቴቶች ተካሂደዋል። እነዚህ ምክክሮች ከሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ከሲቪል ማህበራት፣ ከማህበረሰብ አባላት፣ ከሴቶች ቡድኖች እና ከባህላዊ እና የሀይማኖት አባቶች የተወከሉ ተሳታፊዎች የተገኙበት ነበር። ምክክሮቹ የተካሄዱት በተለያዩ ደረጃዎች ከሚገኙ ተዋናዮች ግብዓት ለማሰባሰብ እንዲሁም በሴቶች፣ ሰላምና ጸጥታ አጀንዳ ላይ ግንዛቤን ለመፍጠር ነበር። የመጨረሻው ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በ2015 (እ.ኤ.አ.) ተቀባይነት አግኝቷል።

## 3. የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን ያለ ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር መተግበር

በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ራሱን የቻለ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ከማዘጋጀት ይልቅ፣ እንደ አማራጭ አንዳንድ አገሮች የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን ከሌሎች ሀገራዊ ወይም አካባቢያዊ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶች እና ፖሊሲዎች ጋር ማዋሃድን መርጠዋል። **ኮሎምቢያ** በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ያላፀደቀች አገር ስትሆን፣ ነገር ግን በኮሎምቢያ መንግሥት እና በ FARC-EP መካከል የተደረገ የሰላም ስምምነት በሥርዓተ-ፆታ ላይ ከ100 በላይ ድንጋጌዎችን ያካተተ የሥርዓተ-ፆታ አመለካከትን ተግባራዊ ያደረገች አገር ምሳሌ ነች። የሴቶች ድርጅቶችም በግጭት የተጎዱ ሰዎችን መብት የሚመለከት ህግ እንዲወጣ በማበረታታት ውጤታማ ሆነዋል።[29] በተጨማሪም፣ የሴቶች ድርጅቶች እና ንቅናቄዎች ግንዛቤን በመፍጠር እና የማዘጋጃ ቤት የድርጊት መርሃ ግብሮችን ከአካባቢ አስተዳደር ጋር በማቀናጀት አጀንዳውን አካባቢያዊ አድርገውታል።[30]

**እስራኤልም** የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን ብሄራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ሳታወጣ ተግባራዊ አድርጋለች። ይህንንም ያደረገችው በብሔራዊ ህግ እና የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ጉዳዮችን በሌሎች ሀገራዊ ዕቅዶች እና ፖሊሲዎች ውስጥ በማካተት እንዲሁም በአለም አቀፍ መድረክ ለዓላማው ጥብቅና በመቆም ነው። የእስራኤል ሲቪል ማህበረሰብ ግን አሁንም አጀንዳውን በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር እንዲፀድቅ ይደግፋል። ምንም እንኳን መንግስት በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ላይ የሚሰራ ቡድን መቋቋሙን ቢያሳውቅም፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተጨባጭ በመንግስት ተቀባይነት ያላገኘውን ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አርቅቀዋል።[31] **በፓኪስታን**፣ በመንግስት ውስጥ ባለው የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ወሠን ላይ ባሉ የተለያዩ አመለካከቶች የተነሳ፣ የሴቶች ልማት ሚኒስቴር በምትኩ በሴቶች ማብቃት ላይ የተጠናከረ የድርጊት መርሃ ግብር ለማዘጋጀት ወስኗል። ከሴቶች፣ የሰላም እና የጸጥታ አጀንዳ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በሴቶች ማብቃት ዙሪያ ያሉትን ሁሉንም ቁርጠኝነቶች አንድ ላይ በሚያገናኝ ሰፊ ዕቅድ ውስጥ ይካተታሉ።

ራሱን ችሎ የቆመ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ከማዘጋጀት ይልቅ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮችን ወደ ነባር ዕቅዶች እና

[29] Steinberg et al. (2015) Implementation of UN Security Council Resolution 1325 in Israel. Implementing and Monitoring National Action Plans: Strategies of Women's Organizations: https://il.boell.org/sites/default/files/nap-_strategies_of_womens_organizations.pdf

[30] Global Network of Women Peacebuilders (2013) *Implementing Locally, Inspiring Globally: Localizing UNSCR 1325 in Colombia, Nepal, the Philippines, Sierra Leone, and Uganda*: https://gnwp.org/wp-content/uploads/GNWP-Implementing-Locally-Inspiring-Globally-Localizing-UNSCR-1325-in-Colombia-Nepal-the-Philippines-Sierra-Leone-and-Uganda-2013.pdf

[31] Global Network of Women Peacebuilders (2013) *Implementing Locally, Inspiring Globally: Localizing UNSCR 1325 in Colombia, Nepal, the Philippines, Sierra Leone, and Uganda*: https://gnwp.org/wp-content/uploads/GNWP-Implementing-Locally-Inspiring-Globally-Localizing-UNSCR-1325-in-Colombia-Nepal-the-Philippines-Sierra-Leone-and-Uganda-2013.pdf

ስትራቴጂዎች ማቀናጀት አነስተኛ ሃብታትን (resources) ሊፈልግ የሚችል ሲሆን ሰላምን፣ ጸጥታን እና ልማትን በተመለከተ ሁሉም ዋና ዋና ዕቅዶች እና ስትራቴጂዎች የስርዓተ-ፆታ አመለካከቶች እንዲያካትቱ ያግዛል። እንዲሁም የሥራ ድግግሞሽን ለማስወገድ እና የፖሊሲውን ወጥነት ለማረጋገጥ ይረዳል። ይሁን እንጂ፣ የዚህ አካሄድ ጉዳቱ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን የሚመለከቱ ጉዳዮች ያለ እውነተኛ ቁርጠኝነት እና ባለቤትነት በነባር እቅዶች ላይ “ተጨማሪዎች” ሊሆኑ ይችላሉ። ራሱን ችሎ የቆመ  የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በአጠቃላይ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አካባቢ ያለውን የሂደት ለውጥ ለመቆጣጠርና ለመገምገም እና መረጃን ለመሰብሰብ ቀላል ያደርገዋል። በተጨማሪም አማራጭ አካሄድ ከተመረጠ እና የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች በነባር ዕቅዶች ውስጥ ብቻ ከተዋሃዱ፣ ከሀብት ድልድል አንፃር ጨምሮ፣ በዕቅዱ ውስጥ ባሉ ሌሎች ተግባራት ሊዋጡ ወይም ሊጨፈለቁ ይችላሉ።[32] የሰላም ስምምነቱ የሥርዓተ-ፆታ ድንጋጌዎች አፈፃፀም ከስምምነቱ አጠቃላይ ትግበራ ይበልጥ ያዘገመ በሆነበት **በኮሎምቢያ** ውስጥ ይህ ሁኔታ ነበር።[33]

## 4. በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ላይ ያሉ ችግሮች እና የመውጫ መንገዶች

ሂደቱ እንዴት መካሄድ እንዳለበት የሚቀርቡ የተለያዩ አመለካከቶች በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት ሂደትን ሊያዘገዩ ወይም ችግር ሊሆኑ ይችላል። **በደቡብ አፍሪካ** የመጀመሪያው አውደ ጥናት ውይይት ከተደረገ በኋላ ሂደቱ ለብዙ አመታት ቆሞ ነበር። ሆኖም ግን፣ ስለ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አስፈላጊነት፣ የመሪ ኤጀንሲ ምርጫ እና የመርሃ ግብሩ ትኩረት ላይ ከተደረጉ ውይይቶች እና በሲቪል ማኅበረሰቡ ከተካሄደው የጥብቅና ስራ በኋላ፣ ከተለያዩ የመንግስት ሴክተሮች በቂ የፖለቲካ ፍላጎት የተገኘ ሲሆን ሂደቱም በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ተጀምሯል። **በፓኪስታን** የሴቶች የማብቃት ሚኒስቴር በመንግስት ውስጥ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ላይ ባሉ የተለያዩ አመለካከቶች የተነሳ፣ ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮችን የሚያጠቃልል ሰፊ የድርጊት መርሃ ግብር በሴቶች ላይ ማዘጋጀት የተሻለ እንደሆነ ተመልክቷል።

በአጠቃላይ ሴቶችን የማብቃት እና የፆታ እኩልነት ጉዳዮችን ለመፍታት **የፖለቲካ ፍላጎት እጦት** እና የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ከሰላም እና ግጭት ጉዳይ ይልቅ "የሴቶች ጉዳይ" ብቻ አድርጎ መመልከቱ የሴቶችን፣ የሰላም እና የጸጥታ አጀንዳን የመተግበር አስፈላጊነትን ወደ ማሳነስ ያመራል።[34] ስለዚህ የሴቶችን ተሳትፎ በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ውስጥ እና በተለይ ደግሞ ከሰላምና ጸጥታ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ውስጥ የማሳደግን አስፈላጊነት መደገፍ ያስፈልጋል።

**የመሪ ኤጀንሲ ወይም ኃላፊነት የሚሰጠው ሚኒስቴር መምረጡ** የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ፍጥነትንም ሊነካ ይችላል። ይህ ከሰሃራ በታች የሚገኙ 15 ሀገራትን በመወከል በናይሮቢ ሲምፖዚየም[35] ተሳታፊዎች እውቅና ያገኘ ሲሆን፣ ተሳታፊዎቹም ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች በስርዓተ-ፆታ ወይም በሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ስር ሲቀመጡ አንዳንድ ጊዜ ዕቅዱ በአጠቃላይ ለብሄራዊ ጸጥታ ስትራቴጂዎች ያለውን ፋይዳ የሚጎዳ ምልክት እንደሚያስተላልፍ ገልጸዋል። በመሆኑም፣ እንደ የውጭ ጉዳይ ወይም የመከላከያ ሚኒስቴር ያሉ ሌሎች ሚኒስቴር መ/ቤቶችን ለብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር እንደ መቀመጫ ኤጀንሲዎች መጠቀም ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩን ለማዘጋጀት እና ለመተግበር ፖለቲካዊ ፍላጎትን ለማሳደግ እንደ አንድ መንገድ ይታያል።

በዕቅድ አወጣጥ ሂደቱ ውስጥ ከሁሉም ተሳታፊ ተዋናዮች ጋር **ቅንጅት እና ግንኙነት/ተግባቦት በመመስረት**፣ ሁሉን-አቀፍ እና ተጨባጭ ዕቅድ መፍጠር ትልቅ ችግር ሊሆን ይችላል። **በላይቤሪያ**፣ አስፈፃሚ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ከትግበራው ምዕራፍ በፊት ስላላቸው ኃላፊነት በበቂ ሁኔታ አልተነገራቸውም ነበር፣ ይህም ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በአንዳንዶቹ መ/ቤቶች ቀዳሚነት እንዳይሰጠው አድርጓል።[36] በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደት ውስጥ በግብረ-ኃይሎች ወይም በኮሚቴዎች ውስጥ ሰፊ ተሳትፎን ማረጋገጥ መረጃ ወደ ሁሉም ባለድርሻ አካላት መድረሱን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። **ቡሩንዲም** ለሁሉም የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አስፈጻሚ አካላት አመታዊ ክፍት ቀናትን (Open Days) በማዘጋጀት ተዋናዮች ቅድሚያ በሚሰጧቸው እና ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ መረጃ እንዲጋሩ

[32] UN Women (2012) *Women and Peace and Security: Guidelines for National Implementation*: https://www.unwomen.org/-/media/headquarters/attachments/sections/library/publications/2012/10/wpssourcebook-02b-planonwomenpeacesecurity-en.pdf?la=en&vs=1154

[33] Special Report of the Kroc Institute and the International Accompaniment Component, UN Women, Women’s International Democratic Federation, and Sweden, on the Monitoring of the Gender Perspective in the Implementation of the Colombian Final Peace Accord (2018) https://kroc.nd.edu/assets/297624/181113_gender_report_final.pdf

[34] Women’s International League for Peace and Freedom (2020) *UNSCR 1325 at 20 Years: Perspectives from Feminist Peace Activists and Civil Society*: https://www.wilpf.org/wp-content/uploads/2020/11/WILPF_UNSCR-1325-at-20-Years_Web.pdf

[35] Nairobi Symposium: Maximizing Impact of Women, Peace, and Security Policies in Africa was organized by the Institute for Inclusive Security, University of Nairobi and Cordaid in July 2014. Conference report: http://www.inclusivesecurity.org/wp-content/uploads/2015/02/Nairobi_Symposium_Conf_Report.pdf.

[36] ibid.

በማድርግ  የግንኙነት/ተግባቦት እና የእውቀት መጋራት ችግርን በትግበራው ምዕራፍ ላይ ቀርፋለች።[37]

በብዙ አገሮች **የሲቪል ማህበረሰብ በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ውስጥ በበቂ ሁኔታ አልተካተተም**። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች  ተሳትፎ በሂደቱ ውጤት ላይ ተጨባጭ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅም የሌለው ለምልክት ወይም ለታይታ የሚደረግ ሊሆን ይችላል።[38] የሲቪል ማህበረሰቡ በሂደቱ ውስጥ ከጅምሩ ተሳታፊ የሚሆንበት ትርጉም ያለው መንገድ ሊመቻችለት እና በአገራዊ እና አካባቢያዊ ጥያቄዎች ላይ ላለው እውቀት በቂ ዋጋ ሊሰጠው ይገባል። ይህንን ችግር ለማስወገድ ጥሩ ተሞክሮዎች በክፍል 2.3 ቀርበዋል። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በየጊዜው የሚያነጋግሯቸውን እና ስለ ሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊነትን የሚሞገቱላቸውን የመንግስት ተወካዮችን በመለየት ይህንን ችግር ለማስወገድ በንቃት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።[39]

**በታይላንድ** ውስጥ እንደታየው ሁኔታ የብሔራዊ እና የአካባቢ ባለስልጣናት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስለሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ እና በአጀንዳውም ስላሉት ዋና ጉዳዮች በጣም ውስን ግንዛቤ ሊኖራቸው ይችላል።

የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን አግባብነት ግጭት ውስጥ ባሉ አገሮች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሰላማዊ አገሮች ውስጥ እና ከግጭት በኋላ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥም መረዳት የአጀንዳውን ሙሉ አቅም ለመጠቀም አስፈላጊ ነው።[40] በመሆኑም በሂደቱ  ተደራሽ የሆኑ ቁሳቁሶችና መረጃዎች በስፋት እንዲዳረሱ እና በአተገባበሩ ወቅት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደት አካል ሆነው እንዲከናወኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው።**በሰለሞን ደሴቶች (Solomon Islands)** ለሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ግብዓት ለመሰብሰብ ታቅዶ በተዘጋጀው ሀገር-አቀፍ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ጉባኤ የተሳታፊውን በቂ እውቀት ለማረጋገጥ ከሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ጋር በተያያዙ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በርካታ የውይይት ክፍለ ጊዜዎች ተካትተዋል። እንደ **ጓቲማላ** ባሉ በብዙ ሀገራት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ክፍል (ዩኤን ውሜን) ሀገራቱ የሚሰሯቸውንና የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደቶች አካል የሆኑትን የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ደግፏል። ቁሳቁሶችን ወደ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች መተርጎም በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ላይ ግንዛቤን ለመደገፍ እና ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ትግበራን ለማጎልበት ጥሩ መንገድ እንደሆነም ተለይቷል።[41]

**የገንዘብ እና ሌሎች ሀብታት (resources) እጥረት** የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ግስጋሴን ሊያደናቅፍ ይችላል። የታቀዱ ተግባራት መሰረዝ ሊኖርባቸው ይችላል ወይም ግስጋሴው ሙሉ በሙሉ ሊቆም ይችላል። ይህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ለመንግስት ብቻ ሳይሆን፣ ለመተግበርና የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የገንዘብ ግብዓቶች ወይም አቅማቸው ውስን ሊሆን የሚችሉ መሰረታዊ ድርጅቶች እና ኔትዎርኮች (grassroots organizations and networks) ሆነው ነገር ግን በሂደቱ ውስጥ ተሳትፎአቸው ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ለሚያመጣ ለእነዚህም ጭምር ነው።[42]

ሌላው ተለይቶ የታወቀው ችግር **በአካባቢ ደረጃ ያሉ ጥያቄዎችን እና ስጋቶችን በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሮች ውስጥ ማካተትን** የተመለከተነው። ይህን ችግር ማስቀረት የሚቻለው የአካባቢያዊ የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮችን በሂደቱ ውስጥ በማካተት እና ድጋፍ በማድረግ እና የአካባቢ ጥያቄዎችን ያገናዘበ የመነሻ ጥናት በማካሄድ ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ጥሩ ልምድ **ከሰለሞን ደሴቶች** የመጣው እና ከ100 የሚበልጡ  ከመላው አገሪቱ የተውጣጡ ሴቶች የተሳተፉበት የሴቶች፣ የሰላም እና የጸጥታ ጉባኤ ሲሆን፣ በጉባኤው ላይ ተሳታፊዎቹ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ላይ የሰለጠኑበት፣ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ቅድሚያ የሚሰጣቸው እና ለድርጊት መርሃ ግብሩ ረቂቅ የሚሆኑ ጉዳዮች እና ተግባራት ተለይተው የታወቁበት እና የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር አስፈላጊነት ላይም ስምምነት የተደረሰበት ነበር። ለስድስት ግዛቶች ስለ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር እና በግዛቶቹ ውስጥ ስለ ሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ስራዎች መረጃን ለመለዋወጥ አውደ ጥናት ተዘጋጅቷል። ይህም ለስድስት ግዛቶች ግዛታዊ የሥራ እቅዶች ከአካባቢያዊ ጥያቄዎች ጋር እንዲዘጋጁ አስችሏል። በተመሳሳይ መልኩ፣ **በናይጄሪያ** 11 ስቴቶች የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን ከመንግስት የድርጊት መርሃ ግብር ጋር አካባቢዊ አድርገዋል እና 5 የአካባቢ መስተዳድር ስፍራዎች የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ከፀደቀ በኋላ የአካባቢያቸውን የድርጊት መርሃ ግብር አሳትመዋል።[43]

---

[37] ibid.

[38] Steinberg et al. (2015) *Implementation of UN Security Council Resolution 1325 in Israel. Implementing and Monitoring National Action Plans: Strategies of Women's Organizations*: https://il.boell.org/sites/default/files/nap-_strategies_of_womens_organizations.pdf

[39] ibid.

[40] Women's International League for Peace and Freedom (2020) *UNSCR 1325 at 20 Years: Perspectives from Feminist Peace Activists and Civil Society*: https://www.wilpf.org/wp-content/uploads/2020/11/WILPF_UNSCR-1325-at-20-Years_Web.pdf

[41] Global Network of Women Peacebuilders (2013) *Implementing Locally, Inspiring Globally: Localizing UNSCR 1325 in Colombia, Nepal, the Philippines, Sierra Leone, and Uganda*: https://gnwp.org/wp-content/uploads/GNWP-Implementing-Locally-Inspiring-Globally-Localizing-UNSCR-1325-in-Colombia-Nepal-the-Philippines-Sierra-Leone-and-Uganda-2013.pdf

[42] Cordaid and Global Network of Women Peacebuilders (2014) *Financing for the Implementation of National Action Plans on UN Security Council Resolution 1325*: https://gnwp.org/financing-naps/

[43] International Alert & UN Women Nigeria. *Women, Peace and Security in Nigeria* (webpage): https://wpsnigeria.net/

በመጨረሻም፣ በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዕቅድ እና ትግበራ ላይ **የወንዶች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑ** ችግር ሊፈጠር ይችሏል። **በታይላንድ** ከሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ጋር በተያያዙ ተግባራት ላይ የወንዶች ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በዕቅድ ደረጃ ሊታሰብበት እንደሚገባ ተስተውሏል። በተመሳሳይ **በኡጋንዳ** ለሴቶች ማብቃት እና ተሳትፎ የሚሟገቱ የወንዶች ቁጥር ዝቅተኛ መሆን በትግበራው ምዕራፍ ላይ እንደ ችግር ተወስዷል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ወንዶች በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳ ላይ ግንባር ቀደም ሚና እንዲኖራቸው ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ከማዘጋጀት ሂደት ጋር ተያይዘው ከሚመጡ ችግሮች በተጨማሪ፣ በአፈፃፀሙ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ በርካታ ችግሮች ስላሉ በሂደቱ መጀመሪያ ላይ ሊታሰብባቸው ይገባል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ዋና ዋና ችግሮች ቀደም ብለው ተብራርተዋል፡- እነዚህም ለብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ትግበራ በቂ ሃብታትን መመደብ፣ ለድርጊቶች ተጨባጭ አመላካቾችን ማስቀመጥና የክትትል እና የግምገማ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፤ እና የሲቪል ማህበረሰብን ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ናቸው። ከዚህም በላይ፣ ዕቅዱ ከፀደቀ በኋላ ከመዘንጋቱ ይልቅ በአግባቡ መተግበሩን ማረጋገጥ የብዙ አገሮች ቀጣይነት ያለው ችግር ነው። ይህም ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን እንደ ቀስ-በ-ቀስ አዳጊ እና በየጊዜው የሚታደስና የሚሻሻል ሰነድ አድርጎ በማዘጋጀት ሊፈታ ይችላል። አፈጻጸሙ በቂ ትኩረትና ሃብታት (resources) እንዲሰጠው ለማረጋገጥም ብሄራዊ መርሃ ግብሩን ከነባር ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ጋር ማቀናጀትና ማስተሳሰር አስፈላጊ ነው።[44] ለትግበራ ስራዎች ግልፅ የሆነ የኃላፊነቶች ክፍፍል መደረጉ በሴቶች፣ ሰላምና ጸጥታ ላይ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብሩ በተሳካ ሁኔታ መተግበሩን ለማረጋገጥ ያስችላል።

## 5. በኢትዮጵያ በቀጣይ መሰራት ያለበት

በሚያዝያ 2019 (እ.ኤ.አ.)፣ የኢትዮጵያ መንግስት የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን በነሀሴ 2020 (እ.ኤ.አ.)[45] ለማዘጋጀት ቃል ገብቷል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ለማዘጋጀት ዝግጅት ተጀምሯል። ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ቀደም ሲል የቀረቡት ሁሉም ችግሮች በኢትዮጵያ የብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ሂደት ማቀድ ውስጥ ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል። የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሂደቱን የመምራት ሥልጣን ተሰጥቶታል። የሰላም ሚኒስቴር፣ የመከላከያ ሚኒስቴር ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር ፣ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር እና የፍትህ ሚኒስቴር ጨምሮ ሌሎች የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መ/ቤቶች የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ላይ መሳተፍ ይኖርባቸዋል። የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ ሥርዓት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች መተግበር ያለበት መሆኑን ለማረጋገጥ በሂደቱ ውስጥ የሁሉም ክልሎች ውክልና እና ተሳትፎ አስፈላጊ ይሆናል። በጀት መመደብን ጨምሮ በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ትግበራ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ተዋናዮች ኃላፊነቶች በግልጽ መለየት አለባቸው።

በኢትዮጵያ የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንደ ቀዳሚነት ሊወሰድ ይገባል። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ክፍል (ዩኤን ውሜን) የኢትዮጵያ ቢሮ (ECO) በሀገሪቱ ውስጥ በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ የሚሰሩ የተለያዩ ተዋናዮችን በተመለከተ ግምገማ አድርጓል። ግምገማው በሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ላይ ለመስራት ፍላጎት ያላቸው እና በብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅት ውስጥ መካተት ያለባቸው ብዙ የሀገር ውስጥ እና አለም አቀፍ የሲቪል ማህበራት እንዳሉ ያሳያል። ነገር ግን፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን ለማረጋገጥ በሁሉም ተዋናዮች ውስጥ የአቅም ግንባታ ስራ ያስፈልጋል። ለሁሉም ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን እንዲያደራጅ እንዲሁም የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ አጀንዳን ለማስተዋወቅ እና ለመደገፍ የሚሆኑ ተግባራትን እንዲያደራጅ የኢትጵያ ቢሮ (ECO) ለሲቪል ማህበር ድርጅት ድጋፍ ያደርጋል።

ከዩኤን ውሜን በተጨማሪ፣ ሌሎች የተመድ ድርጅቶች እና የአፍሪካ ህብረት የሴቶች፣ ሰላም እና ጸጥታ ልዩ መልዕክተኛ (African Union Special Envoy on Women, Peace and Security) ብሔራዊ የድርጊት መርሃ ግብርን በአለም አቀፍ ማዕቀፎች እና ቃል ኪዳኖች ለማቀላጠፍ መደገፍ የሚችሉ ጠቃሚ ባለድርሻ አካላት ናቸው።

---

44 UN Women (2012) *Women and Peace and Security: Guidelines for National Implementation*: https://www.unwomen.org/-/media/headquarters/attachments/sections/library/publications/2012/10/wpssourcebook-02b-planonwomenpeacesecurity-en.pdf?la=en&vs=1154

45 Women's International League for Peace and Freedom (2020) *Call to Action on 2019-2020 commitments* (website): https://www.peacewomen.org/node/103695.

# የንባብ ዝርዝር


African Union Commission (2019) Continental Results Framework. Monitoring and Reporting on the Implementation of the Women, Peace and Security Agenda in Africa (2018-2028). https://au.int/en/documents/20190204/continental-results-framework-reporting-and-monitoring-implementation-women-peace

Global Network of Women Peacebuilders (2013) Implementing Locally, Inspiring Globally: Localizing UNSCR 1325 in Colombia, Nepal, the Philippines, Sierra Leone, and Uganda. https://gnwp.org/wp-content/uploads/GNWP-Implementing-Locally-Inspiring-Globally-Localizing-UNSCR-1325-in-Colombia-Nepal-the-Philippines-Sierra-Leone-and-Uganda-2013.pdf

Global Network of Women Peacebuilders (2017) No Money, No NAP. Manual for Costing and Budgeting National Action Plans on UNSCR 1325. https://gnwp.org/wp-content/uploads/GNWPCostingBudgetingManual_Eng_4web.pdf

Global Network of Women Peacebuilders (2018) From Best Practice to Standard Practice: A toolkit on the Localization of the UN Security Council Resolution 1325 on Women and Peace and Security. https://gnwp.org/localization-toolkit/

PeaceWomen of Women's International League for Peace and Freedom (2013) Women, Peace and Security National Action Plan Development Toolkit. https://www.peacewomen.org/assets/file/national_action_plan_development_toolkit.pdf

UN Women (2012) UN Women Sourcebook on Women, Peace and Security. https://www.unwomen.org/en/digital-library/publications/2012/10/un-women-sourcebook-on-women-peace-and-security#view

UN Women (2012) Women and Peace and Security: Guidelines for National Implementation. https://www.unwomen.org/-/media/headquarters/attachments/sections/library/publications/2012/10/wpssourcebook-02b-planonwomenpeacesecurity-en.pdf?la=en&vs=1154

Women's International League for Peace and Freedom. 1325 National Action Plans (NAPs) (webpage). http://1325naps.peacewomen.org/

## UN WOMEN IS THE UN ORGANIZATION DEDICATED TO GENDER EQUALITY AND THE EMPOWERMENT OF WOMEN. A GLOBAL CHAMPION FOR WOMEN AND GIRLS, UN WOMEN WAS ESTABLISHED TO ACCELERATE PROGRESS ON MEETING THEIR NEEDS WORLDWIDE.

UN Women supports UN Member States as they set global standards for achieving gender equality, and works with governments and civil society to design laws, policies, programmes and services needed to ensure that the standards are effectively implemented and truly benefit women and girls worldwide. It works globally to make the vision of the Sustainable Development Goals a reality for women and girls and stands behind women's equal participation in all aspects of life, focusing on four strategic priorities: Women lead, participate in and benefit equally from governance systems; Women have income security, decent work and economic autonomy; All women and girls live a life free from all forms of violence; Women and girls contribute to and have greater influence in building sustainable peace and resilience, and benefit equally from the prevention of natural disasters and conflicts and humanitarian action. UN Women also coordinates and promotes the UN system's work in advancing gender equality.

UN WOMEN

220 East 42nd Street
New York, New York 10017, USA

www.unwomen.org
www.facebook.com/unwomen
www.twitter.com/un_women
www.youtube.com/unwomen
www.flickr.com/unwomen